# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲ የቋንቋዎች ጥናትና የጆርናሊዝም የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## በወላይታና ጋሞ ምሳሌያዊ ንግግሮች

## የሚታዩ ፆታ ተኮር አዎንታዊና አሉታዊ ተባልጦዎች ትንተና

በ

መዓዛ ከበደ

ሐምሌ 2006

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲ የቋንቋዎች ጥናትና የጆርናሊዝም የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

በአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር

የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ

ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ

አማካሪ

ስንቅነሽ አጣለ

ሐምሌ 2006

አዲስ አበባ

ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምስጋና
አጠቃሎ
ምዕራፍ አንድ
1. መግቢያ
1.1 የጥናቱ ዳራ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 2
1.3. የጥናቱ ዓላማ 2
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ 2
1.5. የጥናቱ ገደብ 2
1.6 የጥናቱ ዘዴ 2
1.6.1 የናሙና አወሳሰድ 3
ምዕራፍ ሁለት 4
2. የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት 4-6
2.1. ምሳሌያዊ ንግግሮች ምንድን ናቸው 6-7
2.2. የምሳሌያዊ ንግግሮች አገልግሎት 7-8
2.3. የምሳሌያዊ ንግግሮች መልእክት 8-9
ምዕራፍ ሶስት… 10
3. የመረጃ ውጤት ትንተና 10
3.1 የወላይታና የጋሞ ምሳሌያዊ ንግግሮች 10
3.2. በወላይታና ጋሞ በሴቶች ላይ አዎንታዊ ተባልጦ የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ትንተና 11
3.3. በወላይታና ጋሞ በሴቶች ላይ አሉታዊ ተባልጦ የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ትንተና 12-16
3.4. በወላይታና ጋሞ በወንዶች ላይ አዎንታዊ ተባልጦ የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ትንተና 16-18
3.5. በወላይታና ጋሞ በወንዶች ላይ አሉታዊ ተባልጦ የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ትንተና 18-19
3.6. በወላይታና ጋሞ በሴቶች ላይ በተመሳሳይ በአሉታዊ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ትንተና 19-20
ምዕራፍ አራት
4. የማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ 21
4.1 ማጠቃለያ 21
4.2 የመፍትሄ ሀሳብ 21-22
አባሪዎች
ዋቢዎች

**ምስጋና**

ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ለስራዬ መሳካት እርማቶችን አስተያየቶችን በመስጠት ለረዱኝ ለመምህሬ ለወ/ሮ ስንቅነሽ አጣለ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ለስራ ያላቸውን ፍቅርና ሰአት አክባሪነታቸውንም ሳላደንቀው አላልፍም፡፡ በመቀጠልም ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቤተ መጻሐፍት ሰራተኞች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል መምህራን በሙሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም ሳይማር ላስተማረኝ ገበሬውን አባቴን አቶ ከበደ ሃይሌን ለእኔ ከማህይምነት መላቀቅ ጅምሩ ካንተ ነው፡፡ በህይወት ባትኖርም ምን ጊዜም ከልቤ በትጠፋምና አመሠግንሃለሁ፡፡ እንዲሁም በቃለ መጠይቅ ለተባበሩኝና አስተያየት ለሰጡኝ የጋሞ እና የወላይታ ቋንቋ ተናጋሪ ጓደኞቼን አመሠግናለሁ በመጨረሻም በአጠቃላይ እንድማር ከጎኔ በመሆን ያበረታቱኝን ቤተሰቦቼን እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አላማ በጋሞና በወላይታ ብሄረሰብ ቋንቋ የወንድና የሴት አዎንታዊ እና አሉታዊ ተባልጦን የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ለይቶ በማመልከት የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በገላጭ የምርምር ዘዴ ሲሆን የጥናቱ የመረጃ ውጤት ትንተና ከቃለ-መጠይቅ ከተገኘው ውጤትና በክለሳ ድርሳናት ከተነሳው ሀሳብ ጋር በማስማማት ጽሁፋዊ ትንተና ተሰጥቷል፡፡ በትንተናው የተደረሰበት ውጤትም በሴቶች ላይ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች በአብዛኛው አሉታዊ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ በመቀጠልም ጥናቱ የሚከተሉትን የመፍትሄ አቅጣጫዎች በመጠቆም ተጠናቋል፡፡ ህብረተሰቡም በሴቶች ላይ በሚነገሩ አሉታዊ ምሳሌዎች ላይ ግንዛቤ እንዲኖረው እና የህብረተሰቡን አመለካከት በመለወጥ ሴቶች ደራሲዎች፣ ጋዜጠኞች፣ ተዋናዮች፣ ገበሬዎች፣ ሀኪሞች፣ አስተዳዳሪዎች፣ እናትም፣ እህትም፣ ሀገርም ከመሆን የማይታቀቡ የህብረተሰብ ክፍሎች እንደሆኑ በመግለጽ በአሉታዊ ይነገሩ የነበሩትን ምሳሌያዊ ንግግሮችን መለወጥ እንደሚገባቸው ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## መግቢያ

ምሳሌያዊ ንግግሮች የአንድን ብሔረሰብ ታሪክ ባህል የደረጃ እድገት የአኗኗር ዘዬን ያንፀባርቃሉ፡፡ ልክ እንደ ማንኛወም ስነ- ቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ ቅርሶች ናቸው፡፡ምሳሌያዊ ንግግሮች ከስነ- ቃል /ኪነ-ቃል /ዘርፎች  እንደመሆናቸው መጠን በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍ ያለ ድርሻ አላቸው ምክንያቱም ሰዎች ጠለቅ ባለ መንገድ ሀሳባቸውን ሳያንዛዙና ሳያሰፉ ለመግለፅ እንዲሁም አዲስ በሆነ መንገድ በሰዎች አእምሮ ላይ ማሳደር ሲፈልጉ እነዚህን ምሳሌያዊ ንግግሮች ይጠቀማሉ፡፡ በምሳሌያዊ ንግግሮች ሀሳብ የሚተላለፈው ቁጥብና ምርጥ በሆኑ ቃላት ተከሽኖ ነው፡፡ንግግሩ ውበትና ጣዕም እንዲኖረው ያደርጋሉ፡፡ በምሳሌነት የቆሙት ጉዳዮች ከሰዎች ከእለት ኑሮ ጋር በተቆራኙ ነገሮች ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም በሚነገሩት ነገሮች ላይ አፅንኦት ለመስጠት ያገለግላሉ፡፡የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በወላይታና በጋሞ ብሄረሰብ በወንዶችና በሴቶች መካከል አዎንታዊና አሉታዊ ተባልጦ የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ትንተና ላይ ሆኖ በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው፡፡

በመጀመሪያ ጠቅላላ የጥናቱ አካሄድ ይቀርባል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ የተዛማጅ ፅሁፍ  ቅኝት ይቀርባል ፡፡ በሶስተኛው ምዕራፍ የዚህ ጥናት ዋና አካል በሆነው ደግሞ ከተገኘው ቃለ መጠይቅ የጥናቱ ውጤትና ትንተና በፅሁፋዊ ትንታኔ ይቀርባል፡፡በአራተኛው ምዕራፍ የማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች ይሰጣሉ፡፡ በመጨረሻም ዋቢና አባሪዎች ይካተታሉ፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ይህን ጥናት ለመስራት ይረዳኝ ዘንድ የተለያዩ ጥናቶችን በመመልከት ሀሳባቸውን በመውሰድና በማየት የራሴን ስራ ለመስራት ሙከራ አደርጋለሁ፡፡

> የሰው ልጅ በህይወት ገጠመኙ በኑሮውና በስራው የተለያዩ ልማዶችን ወጎችን ያዳብራል፡፡ በጣም ጠቃሚ የሆኑትን ይጠቀምባቸዋል ፡፡ እንዲያውም ኑሮውን ህይወቱን እንዲያጣፍጥለት በየጊዜው ምሳሌያዊ ንግግሮችን ይበልጥ ያበለጽጋቸዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ አቻና ወደር የሌላቸው የትውፊት አካሎች ምሳሌያዊ ንግግሮች ናቸው፡፡ የቀረቡበት ምክንያትና ሰበብም በቃል እየተጠኑ ከእለት ተእለት ኑሮኣችን ትልቅ ትንሽ ሳይባል ባህላችንን ደንባችንን ስነ- ምግባራችን አጠቃለው በያዙት ምሳሌያዊ ንግግሮች እየተጠቀምን ስሜታችንን በማያሻማ ሁኔታ እንገልፃለን ፡፡ ምሳሌያዊ ንግግሮችን የደረሳቸው እከሌ ነው አይባልም ፡፡ምክንያቱም እጅግ ከረጅም ዘመን በፊት ጀምሮ ህዝቡ እንደ ጋራ ሀብት በጋራ ሲጠቀምባቸው በመኖሩ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ምሳሌያዊ ንግግሮች የህዝብ ሃብት ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ምሳሌያዊ ንግግር ለተባለበት ጉዳይ ሲውል ግቡን ይመታል፡፡ነገር ግን አወቅሁ ተብሎ በማያገለግልበት ቦታ ቢደነቅሩት ጠቀሜታ የለውም፡፡ (ደበበ፣ 1999)

በየትኛውም ማህበረሰብ ሴቶች በሁሉም የስራ መስክ እንዲሁም ማህበራዊ ህይወት እዚህ ቀረ የማይባል ድርሻ አላቸው ፡፡ ከቤተሰቦቻቸው ጀምሮ እስከ ማህበረሰቡ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በአብላጫው የህይወትን ውጣ ውረድ የሚወጡት ሴቶች እህቶቻችን ናቸው፡፡ ቀደም ሲል በሀገራችን በፅሁፍ በበለፀገው የአማርኛ ቋንቋም ሆነ ሌሎች በፅሁፍ ላይ ባልዋሉ የሀገራችን ቋንቋዎች ምሳሌያዊ ንግግሮች በአብዛኛው ሴቶችን ከማሞገስ ይልቅ በማሳነስ ወይም ችግር ፈጣሪና አጥፊዎች በመሆናቸው ላይ የሚነገሩ ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት የሰዎችን አመለካከት ለማቅናትም ሆነ ለማሳደግ በጥናት የተረጋገጠ ተጨባጭ መረጃ ለማግኘት ሆኖ በወላይታና በጋሞ ብሄረሰብ በወንዶችና በሴቶች መካከል አዎንታዊና አሉታዊ ተባልጦ የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ለማወቅ ብሎም ለመተርጎምና ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለመስራት ያነሳሳኝ ምክንያት በአብዛኛው በአማርኛ ቋንቋ ሲነገሩ የምንሰማቸው ምሳሌያዊ ንግግሮች ሴቶችን የሚያበረታቱ ሳይሆን በሴቶች ላይ ተፅእኖ ፈጣሪ መሆናቸው ነው፡፡ሌላው በሌሎች ቋንቋዎች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ተመሳሳይ ይዘት እንዳላቸው ለማየትና ለሌሎች ተደራሽ ለማድረግ ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ በወላይታና በጋሞ ብሄረሰብ በወንዶችና በሴቶች መካከል አዎንታዊና አሉታዊ ተባልጦ የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመሰብሰብና በመተንተን ልዩነቶችን ማሳየት ነው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚከተሉትን ፋይዳ ያስገኛል ተብሎ ይገመታል፡፡

ሀ. በሴቶች ላይ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን አመለካከት ለመቀየር ይጠቅማል፡፡

ለ. ከዚህ በኋላ በዚህ ዙሪያ ለሚደረጉ ሌሎች ጥናቶች መነሻ የሚሆኑ ሃሳቦችን በመጠቆም ረገድ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይቻላል፡፡

ሐ. በሴቶች ላይ በአሉታዊ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች በርካታ መሆናቸውን ለማወቅ ይጠቅማል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ገደብ

በሀገራችን ቋንቋዎች በተለያዩ ጉዳይ ላይ የሚነገሩ በርካታ ምሳሌያዊ ንግግሮች አሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ላይ በሙሉ የሚያተኩር ተደርጎ ሊታይ አይገባም፡፡የዚህ ጥናት ትኩረት በወላይታና በጋሞ ብሄረሰብ በወንዶችና በሴቶች መካከል አዎንታዊና አሉታዊ ተባልጦ የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ለይቶ ለማወቅና ያላቸውን ልዩነት በማሳየት ላይ ብቻ ያተኮረ ይሆናል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱን ለማካሄድ የምንጠቀምበት ዘዴ በቃለ-መጠይቅ ሲሆን በገላጭ የምርምር ዘዴ ውስጥ የሚታቀፈውን የይዘት ትንተና ስልት ነው፡፡ በዚህ በመጠቀም አሰራሩንም በሚመለከት

ሀ. ምሳሌያዊ ንግግሮችን በወላይታና በጋሞ ብሄረሰብ ቋንቋ መሰብሰብ ነው፡፡

ለ. ከተሰበሰቡት ምሳሌያዊ ንግግሮች የወንድና የሴት ተባልጦ የሚያሳዩትን መለየት

ሐ. በወላይታና በጋሞ ብሄረሰብ ቋንቋ በፅሁፍ ማስፈር ነው፡፡
መ.ትርጉሙን በአማርኛ ቋንቋ መፃፍ ነው፡፡

### 1.6.1. የናሙና አወሳሰድ

የመረጃ ምንጮች የሆኑት የጋሞና የወላይታ ብሄረሰብ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው ፡፡ ለመረጃ ሰጪነት የተመረጡበት ምክንያት የቋንቋው ባለቤቶች አፍ በፈቱበት ቋንቋ ላይ የተሻለ እውቀት ሊኖራቸው ስለሚችል የበለጠ ተመራጮች ይሆናሉ፡፡

**የመረጃ ማሳሰቢያ ዘዴው የተመረጠበት ምክንያት ቃለ -** መጠይቅ ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ተጨባጭ የሆኑ መረጃዎችን በአካል ተገኝቶ በራሳቸው በቋንቋው ባለቤቶች በተለይም የእድሜ ባለፀጋ ከሆኑት ለመገንዘብ የተሻለ በመሆኑና ተጠያቂዎቹ ማንበብ መጻፍ የማይችሉ ሊኖሩ ስለሚችሉ የሚነረውን በትክክል ማስታወሻ ለመያዝ አመቺ በመሆኑ ነው፡፡

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## 2. የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት

ለዚህ ጥናት አጋዥ የሆኑ ምሳሌያዊ ንግግሮች ዙርያ በመስኩ በለሞያዎች የተሰሩ ስራዎችን እንደሚከተለው እቅኛለሁ፡፡

ወርቁ ከበደ፡፡ "የሶማሊኛ ተረትና ምሳሌዎች" ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፡፡ (1973) በኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ለባቺለር ዲግሪ ሟሟያ የቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናታቸው ሂደት የምሳሌያዊ ንግግሮችን ምንነት ጠቀሜታና ትርጉም በመስጠት ይጀምሩና በተለያዩ ምሁራን የሚጠቀሱትን ሃሳቦች አስቀምጠዋል ፡፡ ቀጥሎም በሶማሊኛ ቋንቋ በሁሉም ጉዳዮች ላይ የሚነገሩትን ምሳሌያዊ ንግግሮች ትርጉማቸውን በአማርኛ በመስጠት ተንትነዋል፡፡ በዚህ ውስጥ ስለ ወንድ የበላይነት በሰጡት አስተያየት ላይ ወንድ የሴትን ነገር መስማት የለበትም ሴት እምነት የሌላት ወላዋይ ናት፡፡ የመኖር እድሏም በወንድ በጎ ፍቃድ ላይ የተመሰረተ ነው የሚሉ አባባሎች በምሳሌያዊ ንግግሮች ውስጥ መንፀባረቃቸውን ገልፀዋል፡፡ ጥናቱን ለማድረግ የተጠቀሙበት የመረጃ ማሳሰቢያ ዘዴ ቃለ-መጠይቅ እንደሆነም አስረድተዋል፡፡ ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይነቱን ሳይ በጥናታቸው ውስጥ በመጠኑም ቢሆን በሴቶች ላይ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች አሉታዊ እንደሆኑና በሴቶችና በወንዶች መካከል መበላለጥ መኖሩን አሳይተዋል፡፡ በተጨማሪም በአማርኛ ትርጉም ከመስጠታቸው ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው ያሳየናል፡፡

**መንገሻ ግዛው** ፡፡ "የወላይትኛ ተረትና ምሳሌዎች" ፡፡በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፡፡ (1973) በኢትዮጲያ ቋንቋዎች ስነ ፅሁፍ ለባቺለር ዲግሪ ሟሟያ የቀረበ ጥናት ሲሆን የወላይታን ብሄረሰብ ምሳሌያዊ ንግግሮች ለማስተዋወቅና ስለስራ፣ ስለሴቶች ለተለያዩ ጉዳዮች የሚነገሩትን ምሳሌያዊ ንግግሮች በመሰብሰብ ተመሳሳይነታቸውን እና ልዩነታቸውን በማነፃፀር ትርጉማቸውን በአማርኛ ፅፈዋል፡፡ በአብዛኛው ከአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች ጋር የሚመሳሰሉ መሆናቸውን እንዲሁም ጥሩ አድራጊን የሚያበረታቱ መጥፎውን የሚያጥላሉ እና ጥሩውን ከመጥፎ ለማወዳደር የሚነገሩ እንደሆኑም የተመለከቱበት ነው፡፡

በሴቶች ላይ በሚነገሩት ምሳሌያዊ ንግግሮች ላይ የሰጡት አስተያየት ሴቶች ጨካኞች፣ ብልሆች ፣ አቅመ ደካሞች ፣ግብዞች እንደሆኑ ተደርገው በወላይታ ምሳሌያዊ ንግግሮች እንደሚነገሩ በመግለፅ እና በሌሎችም ብሄረሰቦች መኖራቸው እንደማይቀር በመጥቀስ በብዙ ቦታም ሴቶች ከወንዶች የበታች

ሆነው የሚወስዱ ሆነው ይታዩ እንደነበረ ገልፀዋል፡፡ የጥናታቸው ሂደት በመጀመሪያ የብሄረሰቡን የአኗኗር ሁኔታ የወላይታን የቦታ አቀማመጥ የወላይታን ታሪካዊ ዳራ የምሳሌያዊ ንግግሮች አጠቃቀም በመግለፅ ሲሆን ለጥናቱ የተጠቀሙበት ዘዴም ቃለ-መጠይቅ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ተመሳሳይነት በወላይታ ቋንቋ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ወደ አማርኛ መተርጎም እና በሴቶች ላይ የሚነገሩ አሉታዊ ምሳሌዎች መኖራቸውን መግለጽ ተመሳሳይ ያደርገናል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ፡፡

**ሰለሞን ታደሰ**፡፡ “የአማርኛና የኦሮምኛ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በንጽጽራዊ ጥናት”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (1986) በኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ለባቺለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ሲሆን ፀሃፊው የምሳሌያዊ ንግግሮች ጠቀሜታ፣ እውነታን ብልህ ምክርን የሚያስረዱ አጭርና እምቅ አገላለፅ መሆናቸውን ከተለያዩ ምሁራን ያገኙትን ሃሳብ በማያያዝ የአንድን ህዝብ ምንነት ለመገንዘብ ከማስቻሉም በላይ መልካምና በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ባህልና ወግ ለማስተማር የሰውን ፀባይና ባህሪ ለማረቅ የሰዎችን ቋንቋ ግንኙነት ለማቀላጠፍ በእጅጉ እንደሚረዱና ከዚያም አልፈው የአንድን ማህበረሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሃብት ለይቶ ለማወቅ እንደሚያግዙ ገልፀዋል ፡፡ በተጨማሪም ለምሳሌያዊ ንግግሮች መሰረቱና ምንጩ የማህበሰቡን የአኗኗር ስርዓት እንደሆነ እና ለዚህ ማህበራዊ ስርዓት የሚገለገሉባቸው የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሃብቶች እንደመሆናቸው መጠን የማህበረሰቡ ስርዓትና የአኗኗር ዘይቤ በተለወጠ ቁጥር የምሳሌያዊ ንግግሮችም ቅርፅና ይዘት እንዲሁ እየተለወጠ ይሄዳል፡፡ በማለት አስረድተዋል፡፡ ጥናታቸው የሚያተኩረው በአፋን ኦሮሞ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች በአማርኛ ትርጉም መስጠትና የአባባላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት በማነፃፀር ማስቀመጥ ላይ ነው፡፡የተጠቀሙበት የመረጃ ማሳሰቢያ ዘዴም ቃለ- መጠይቅ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ከአጥኚው አገላለፅ የምንረዳው ምሳሌያዊ ንግግሮች በሚነገሩበት ጉዳይ ላይ ተቀባይነት ያላቸው በመሆናቸውም በየጊዜው ቅርፅና ይዘታቸው መለወጥ እንደሚገባው ሆኖ ሳለ አሁን ባለንበት ወቅት ቀደም ሲል በሴቶች ላይ በአሉታዊ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ለውጥ ሲደረግባቸው አልታየም፡፡

አዲስ ተብለው በሚዘጋጁት ምሳሌያዊ ንግግሮች መጽሐፍት ላይ ቀደም ሲል ሲናገሩ የነበሩት ወንዶችና ሴቶችን የሚያበላልጡ አዎንታዊና አሉታዊ ምሳሌዎች ይታያሉ ፡፡ እነዚህን ለይተን ለማውጣትና ልዩነቶችን ለማስቀመጥ እንዲረዳን በጥናት የተደገፉ መረጃ ሊኖረን ይገባል፡፡ የጥናቱ ተመሰሳሳይነት ከመገኛ ቋንቋ ወደ ተቀባይ ቋንቋ ትርጉም በአማርኛ በመስጠት ላይ እና ምሳሌያዊ ንግግሮች እንደ አስፈላጊነታቸው ለውጥ ሊደረግባቸው ማስፈለጉ ለማሳየት ነው ፡፡

ከላይ የተመለከትናቸው ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይነታቸውን በእያንዳንዱ ጥናት ማጠቃለያ ስር አስቀምጫለሁ፡፡ የሦስቱም ልዩነት ተመሳሳይ በመሆኑ በአጠቃላይ በሁሉም ጉዳዩች ላይ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመውሰድ እንደየ አባባላቸው በመለያየት በአማርኛ ትርጉም መስጠት ሲሆን የእኔ ጥናት ግን በወንዶችና በሴቶች መበላለጥን የሚያሳዩ አሉታዊና አዎንታዊ ምሳሌዎች በርካታ መሆናቸውን ለማሳየትና ፍቻቸውን በአማርኛ መስጠጥና በትንተና ማስቀመጥ ላይ ይሆናል፡፡፡

2.1 ***ምሳሌያዊ ንግግሮች ምንድን ናቸው***

ምሳሌያዊ ንግግሮች እንዲህ ናቸው ብሎ ባጭር ለመተርጎም አስቸጋሪ ቢሆንም ምሁራን የሰጡትን ብያኔ መመልከት ይቻላል፡፡

> *ምሳሌያዊ ንግግሮች አጥር ምጥን ያሉ ጥንታዊ አሻራን የዕለት ተዕለት ገጠመኞችን የሚገልጹና በጊዜና በድንበር የማይወሰኑ ናቸው፡፡ ከሞላ ጎደል በሁሉም ጥንታዊም ሆነ ዘመናዊ ባህል በተማረና ባልተማረውም ማህበረሰብ ይዘወተራሉ፡፡ በአጠቃላይ ምሳሌዎች በስፋት የሚታወቁ የእውነት ቅመሞችን ጨውነትን ምጥንነትን ስሜትን ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው፡፡* **Stone, Jon R (2006)**

ከፀሀፊው አገላለፅ የምንረዳው ምሳሌያዊ ንግግሮች በየትም ቦታ መገኘታቸውንና በጥንታዊም ሆነ በዘመናዊ በተማረውም ባልተማረውም ተዘውትረው የሚነገሩ እንደሆነ ነው፡፡

> *ዘሪሁን ደግሞ እንዲህ ይገልጹታል፡፡ ምሳሌያዊ ንግግሮች ለሀሳብ መቋጫ ማጠናከሪያ ማጉያ ግልፅ ማድረጊያ ይሆናሉ፡፡*

> *ሰዎች በንግግራቸው መሀል ጣልቃ እያስገቡ ምሬታቸውን ምኞታቸውን ሀዘን ደስታቸውን ስለ ህይወት ያላቸውን አመለካከት ያንፀባርቁበታል፡፡ በተጨማሪም ቅሬታቸውን የሚያሳዉቁበት አስነዋሪ ተግባርን የሚነቅፉበት እኩይ ድርጊትን የሚያንቋሽሹበት ሰናዩን የሚያሞግሱበት ባጠቃላይ በማህበራዊ ህይወት ዉስጥ በሚደረጉ ክንዋኔዎች ላይ ሂስ የሚሰጡበት መግለጫ ነው፡፡ ዘሪሁን* (2002)

ይህ አገላለፃቸው ምሳሌያዊ ንግግሮች ለተለያዩ ተግባራት መዋላቸውን ያስረዳናል፡፡

> *"**Jeslaw** እንዲህ ይላሉ፡፡ ''በእጅ ያለ ምሳሌ ከሺ ቃላት ይበልጣል'' ምሳሌዎች ምክርን ተግሳፅን ግልፅ እውነታን የሚገልፁ የህዝብ አባባሎች ናቸው፡፡ የምሳሌዎች መገኛ*

ትዉፊት ስለሆነ በቀላሉ የሚታወሱና በየትውልዱ በዙም ለውጥ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ **Jeslaw (1973)"**

በማለት ከሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር በማያያዝ ነገሮችን በቀላሉ የምንገልፅባቸው በየጊዜው ብዙም ለውጥ የማይታይባቸው መሆናቸዉን ይገልፃሉ፡፡

"Mider, Wolfgang (2004) እንዲህ ይገልፁታል፡፡ ምሳሌያዊ ንግግሮች የተገኙበትን ማህበራዊ ባህላዊ ታሪካዊ እሴቶችና የተፈጥሮ ክስተቶች ጋር በማያያዝ በይነዋል፡፡ በአጠቃላይ ስለ ምሳሌያዊ ንግግሮች ከላይ በቀረቡት ብያኔዎች እንደተረዳነው ምሳሌያዊ ንግግሮች በቦታና በጊዜ የማይወሰኑ ለትውልድ የሚተላለፉ በየጊዜዉ ብዙ ለውጥ የሚያሳዩ የህዝብ ቃል መሆናቸውን ነው፡፡"

ከዚህ የምንረዳው ምሳሌያዊ ንግግሮች ለውጥ የማያሳዩ ቢሆንም መለወጥ የሚችሉ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህ ሲባል ደግሞ በቀላሉ መለወጥ እንደማይችሉ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ ምክንያቱም በብዙ ጊዜ ልምድ የመጣዉን ምሳሌያዊ ንግግር በአንድ ጀንበር ለመለወጥ አዳጋ መሆኑ አይቀርም፡፡ ይሁን እንጂ የወንድና የሴት ተባልጦን የሚያሳዩ አሉታዊ ምሳሌዎችን መለወጥ የሚችል አቅም መፍጠር እስከቻልን የያዝኩትን አለቅም ብሎ ሙጭጭ አይኖርም፡፡

## 2.2 <u>የምሳሌያዊ ንግግሮች አገልግሎት</u>

ምሳሌያዊ ንግግሮች በርካታ አገልግሎት እንዳላቸው የተለያዩ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡

Simpson Jon and Speakesennifer, (1998) እንዲህ ይገልፁታል፡፡

"ምሳሌያዊ ንግግሮች የቋንቋ ነባር ቃላትን የሚይዙና በየትውልዱ የሚከሰቱ አመላካቾችን የሚያንፀባርቁ የሰው ልጅ ቋንቋ እድገትና ታሪክ እንደከርሰምድር ንጣፎች የስልጣኔ ደረጃዎች የሚገልጹ ናቸው፡፡ አገልግሎታቸው ምክርን ለማጎልበት ለማስተማርና መመሪያለማስተላለፍ ነው፡፡ በማለት የሰውልጅ ዘውትር ከሚያከናውናቸው ድርጊቶችና ከቋንቋ እድገት ጋር ያያዙታል፡፡"

ደበበ፣ ደግሞ እንዲህ ይላሉ፡፡ የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች በብዛት ባለ ሁለት ሐረጎች ናቸው፡፡ እነዚህ እንደ ስነ-ቃል ቅርስነታቸው ከሀገራችን በተጨባጭ ሁኔታ ጋር እየተገናዘቡ ለመማሪያ መጽሐፍት ዝግጅት ለድርስትና ስነ-ፅሁፍ እድገትና ብልፅግና ለቲያትርና ለሲኒማ መነሻ ጭብጥ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ በቀድሞ ዘመን የገገሮው መደብ አባላት ምሳሌያዊ ንግግሮችን ለግል ጥቅማቸው ማስጠበቂያ የመበዝበዣ

የመጨቆንኛ መሳርያ አድርገው እንደሚጠቀሙባቸውና ሴቶች በማጀት ብቻ ተከልለው እንዲኖሩ ተጽኖ የሚያደርጉ ምሳሌያዊ ንግግሮችን እንደ ሚጠቀሙ በመግለፅ ያስረዳሉ፡፡ እንደ ፀሐፊው አገላለፅ የምንረዳው የቀድሞ ስርዓት በዘረጋው መንገድ ምክንያት በአብላጫው በሴቶች ላይ የሚናገሩ ምሳሌዊ ንግግሮች አሉታዊ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

ምሳሌያዊ ንግግሮች በሀገር ባህል የፍርድ አስጠጥ ሥነ-ሥርዓት ወይም ሙግት ጊዜም ያገለግሉ እንደነበር የታወቀ ነው፡፡ በጥናት ዘመን የባህላዊ ሙግት እስጥ አገባ ስለሆነ ተሚጋቾች

በላ፡ልበ ልሃ

የአጤ ስርዓቱን

የአብርሃም እራቱ

አልናገረም ሀሰቱን

ሰርክ እውነት እውነቱን

በሚሉ ሀረጎች ይጀምሩና አጫጭር ግጥሞች በምሳሌያዊ ንግግር አስደግፈው የሙግታቸውን ውርድ (ከላይ ወደታች) ይደረድራሉ፡፡ ደበበ (1999)

ይህ የሚያስረዳን እንደየ ሙጉቱ መለያየት በተለያዩ ግጥሞች መልስ እየተሰጠ የፍርድ ስርአቱ የሚከናወን መሆኑን ነው፡፡

2.3 **የምሳሌያዊ ንግግሮች መልእክት**

የምሳሌያዊ ንግግሮች መልእክቶች መሀበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ስነ ልቦናዊ ይዘት እንዳላቸው ደበበ፣ እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ የሚታዩትን አስነዋሪ ባህሪያትን ለመዋጋትና መልካም ስነ ምግባር እንዲዳብር ፍቅር ታማኝነት፣ ትህትና እውነት ሰላም እንዲሰፍኑና ትእግስት እንዲኖር የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ በማለት በቅደም ተከተል በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ ነገሮች በየፈርጁ በምሳሌዊ ንግግሮች እንደሚገለፁ ያብራራሉ፡፡

- ምሳሌያዊ ንግግሮች በህብረተሰቡ መካከል መፈቃቀር መተዛዘን እንዲኖር ማጭበርበር ስስትና ንፍገት እንዲጠፉ ያስገንዝባሉ፡፡
- ህፃናት በስርዓት ተኮትኩተው ማደግ እንደሚያስፈልጋቸው ወላጆችና አሳዳጊዎችን ይመክራሉ ያስጠነቅቃሉ ፡፡
- ጉብዝና ጀግንነትን ያደፋፍራሉ ፡፡ ፍርሃትን ያንኳስሳሉ፡፡
- ህዝብ ከበሽታ እንዲጠነቀቅ በበሽታ ከታያዘ በጊዜው አስፈላጊውን የህክምና ወይም የወጌሻ እርዳታ እንዲጠይቅም ምክር ይለግሳሉ፡፡ ያስተምራሉ፡፡
- ስራ መስራት የሚያስከብር የሚያኮራ ከችግርና ከሃሳብ ነፃ የሚያወጣ መሆኑን ይመክራሉ ያስተምራሉ፡፡
- የጊዜን ክቡርነት በመግለፅ ሕብረተሰቡ ለነገ ሳይል ስራውን በወቅቱ መፈፀም እንዳለበት ይህ ካልሆነ ግን በስራ ፈትነት መታወቅ መከበርና መሞገስ እንደማይገኝ ያስጠነቅቃሉ
- የአፊ ጮሌዎች እውቀትና ችሎታው ሳይኖራቸው የሚመፃደቁትን ለማስጠንቀቅ ይጠቅማሉ፡፡
- የመማር ጥቅምና አስፈላጊነትን አበክረው ያስረዳሉ፡፡
- የመምረጥ ችሎታ የሌላቸውን ሰዎች ይተቻሉ
- ሰዎች ተዘጋጅተው ተሰናድተውና ተጠንቅቀው ካልተቀመጡ አስቸኳይ መፍትሔ የሚፈልግ ጉዳይ ቢደርስ እንደሚቸገሩ ያስገነዝባሉ ሌብነት ዘረፋን ህገወጥ ወንጀሎችን በትዝብት ከማየት ይልቅ ህዝባዊ ቅጣት እንዲኖርም የሚጠይቅ መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡
- ሰዎች ባልፈፀሙት ጥፋት ወንጀለኞች ተብለው ሲያዙ የመቃወሚያ ስልቶች ናቸው፡፡
- ምሳሌያዊ ንግግሮች ርህራሄን የሚጠይቁ ለጥፋተኞች ይቅርታን የሚለምኑ ቂም በቀል እንዲቀር የሚመክሩ ናቸው፡፡ ደበበ፣ (1999)

በማለት በርካታ የተለያዩ መልዕክቶችን እንደሚያስተላልፉ እንረዳለን፡፡ ፀሐፊው በየፈረጁ በብዙ መልክ ምሳሌያዊ ንግግሮች ያላቸውን መልዕክት በዝርዝር ማስቀመጣቸው እውነት ሆኖ ሳለ የሴቶችን ታታሪነትና ጥንካሬአቸውን የሚገልፁ በመልዕክታቸው ውስጥ ያላካተቱበት ምክንያት ብዬ የምገምተው ቀደም ሲል በሴቶች ላይ ሲነገሩ የኖሩት ምሳሌዎች ከአዎንታዊነታቸው ይልቅ አሉታዊነታቸው የጎላ በመሆናቸው ነው፡፡

## ***ምዕራፍ ሦስት***

3. ***የመረጃ ውጤት ትንተና***

በወላይታና በጋሞ ብሔረሰብ በወንዶችና በሴቶች መካከል አዎንታዊና አሉታዊ ተባልጦ የሚያሣዩ ምሣሌያዊ ንግግሮች ሲፈተሹ በምዕራፍ ሁለት ከተነሱት የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት አንፃር ስንቃኛቸው ስለምሣሌያዊ ንግግሮች የተዘረዘሩት ሃሣቦች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሴቶች ላይ የሚነገሩት ምሣሌዎች ምን መልክ እንዳላቸው ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

3.1 ***የወላይታና የጋሞ ምሣሌያዊ ንግግሮች***

በቀጥታ ወደ ምሣሌያዊ ንግግሮች ከመግባታችን በፊት ስለወላይታና ጋሞ ብሔረሰቦች ምንነት በአጭሩ እንመልከት፡፡

«**ወላይታ**» የሚለው ቃል የሕብረተሰቡ መለያ ሆኖ የተገኘውም ወይም የመጣው «**ወላሄታ**» ከሚለው የወላይትኛ ቃል ሲሆን በአማርኛ «**ተቀላቀለ**» ማለት ነው፡፡ የቃሉ ስያሜ የተጠቀሰበት ምክንያት የተለያዩ ጎሳዎች ከተለያዩ አካባቢዎች በመምጣት ጥንታዊ ወላይታን መስርተዋል፡፡ ተብሎ ስለሚገመት ነው፡፡

«**ጋሞ**» በቀድሞ በጋሞጎፋ ከሚገኙ አራት አውራጃዎች አንዱ ነው፡፡ የቃሉ ስያሜ «**አንበሳ**» ማለት ነው፡፡ የወላይታና የጋሞ ቋንቋና ባህል ባላቸው ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ የተነሣ ተመሳሳይ ናቸው፡፡

በማንኛውም ሥፍራ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች በቋንቋው አሰካክ በምሳሌነት የሚጠቀሙባቸው በመካከላቸው የተፈጠሩ ችግሮች ካሉ ሸንጎ ተቀምጠው ለመፍታት የተጣሉትን ለማስታረቅ የግል ብሶታቸውን ለማስረዳት ሲፈልጉ ነው፡፡ እነዲሁም በሥነምግባር ለማበረታታት ፀያፍ ነገሮችን ለማንቋሸሽ ይጠቀሙበታል፡፡ ሕብረተሰቡ የምሣሌያዊ ንግግሮችን ጥቅም ለመግለጽ

«ሴሜሶይ» ሃሰያ ይታና ማይኮና ተፈተስ» ይላሉ፡፡ ይህ ማለት ምሳሌያዊ ንግግሮች ነገርን ባይቆርጡም ያሳጥራሉ ማለት ነው፡፡

3.2 **በወላይታና በጋሞ በሴቶች ላይ አዎንታዊ ተባልጦ የሚያሣዩ ምሳሌያዊ ንግግሮች**

ከዚህ በመቀጠል በወላይታና ጋሞ ምሳሌያዊ ንግግሮች በሁለቱም ቋንቋዎች በመለየትና ፍቺአቸውን በአማርኛ በመስጠት እንዲሁም ከምሣሌያዊ ንግግሮች ውስጥ የተወሰኑትን በምሣሌነት በመውሰድ በትንተና ይቀርባሉ፡፡

1. አዲስ ግኮ ማጫናይ አይሰሱ (ጋሞ)

   ትርጉም፣ ሁኔታው ከፈቀደላት ሴት ታስተዳድራለች፡፡
2. ኩቶ ሹኪን አሾ ኩሼ አይኪን መቾ (ጋሞ)

   ትርጉም፣ ዶሮ አርደው ሥጋ በእጅ ይዘው ሚስት፡፡
3. ጦስ ጦሬ እምን አማራ ቀንጢ ኪኤስ፡፡ (ጋሞ)

   ትርጉም፣ እግዚአብሔር የፈጠረውን ብልት አማራ ቆርጦ ይጥላል፡፡
4. አዋይ ዶሲያ ናአይ ሳይታወሱ፡፡ (ጋሞ)

   ትርጉም፣ አባትዋ የሚወዳት ልጅ በሁሉም ነገር ቀዳሚ ነች፡፡
5. ማጫ ሞገስና ቦና፡፡ (ወላይታ)

   ትርጉም፣ ሴት ወደቀብር አትጠጋም፡፡
6. ማጫ ሄዩ ቱማ ግን የኬስ፡፡(ወላይታ)

   ትርጉም፣ ሴት እውነቱ ሲደርስ ታደቅሳለች፡፡

<<ሁኔታው ከፈቀደለት ሴትም ታስተዳድራለች>> የሚለው ሴቶች ሀገር መምራት የሚችሉ ጠንካራ አቅምና አስተሳሰብ ያላቸው መሆናቸውን የሚገልጽና እዚህ ደረጃ ለመድረስ ሁኔታው ያልተመቻቸላቸው መሆኑን ያስረዳናል፡፡

<<ዶሮ አርደው ሥጋ በእጅ ይዘው ሚስት፡፡>> ዶሮ በሀገራችን ተወዳጅ ባህላዊ ምግብ ነው፡፡ ለመሥራት ሞያ ያስፈልገዋል፡፡ ስለዚህ አጣፍጦ ለመብላት ወሳኟዋ ሴት ናት ያለስዋ አይሆንም፡፡

<<እግዚአብሔር የፈጠረውን የሴት ብልት አማራ ቆርጦ ይጥላል>> የሚለው ሴቶች ግርዛት እንዳይፈፀምባቸው የሚመክር መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

<<አባትዋ የሚወዳት ልጅ ሁሉም ነገር ይሳካላታል።>> አባትዋ የሚወዳት ልጅ ትበረታታለች ወይም የተሻለ ነገር ትሠራለች ነው። ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ሴቶች ተጠይነታቸው በወንዶች ስለሚገለጽና ጥቃትም የሚደርስባቸው በወንዶች ስለሆነ በተጨማሪ በአባታቸውም ሲጠሉ ከወንዶች ተራ ይመድቡትና ገና ከጅምሩ ምንም ነገር ከመሥራት ይታቀባሉ፣ ይፈራሉ ይሸማቀቃሉ።

<<ሴት ወደቀብር አትጠጋም።>> የሚለው ሴቶች አዛኞች እንደሆኑና የሰውን መጥፎ ነገር እንደማይፈልጉ የሚገልጽ ነው።

<<ሴት እውነቱ ሲደርስ ታለቅሳለች።>> ይህ የሴቶችን ሀቀኝነት የሚገልጽ ሆኖ በምንም ነገር ቢታለሉ ወይም ስህተት ቢሰራባቸው እውነትን አጥብቀው መፈለጋቸውንና ሲያሸንፉ ደስታቸው ከመጠን በላይ ሲሆን በለቅሶ እንደሚገልፁት ያሳየናል።

3.3. **በወላይታና ጋሞ በሴቶች ላይ አሉታዊ ተባልጦ የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮች**

1. ማጨስ ማቲ ሞከና። (ጋሞ)

    ትርጉም፣ ሴት በቆመችበት ሳር አይበቅልም።

2. ማጫ ናኢ የሌቲን ሄዞ ጊዜ አለል ጌቴ ኦዴ የሌቲን ኦይዱ ጊዜ አለል ጌቲ። (ጋሞ)

    ትርጉም፣ ሴት ስትወለድ ሦስት ጊዜ እልል በሉ ወንድ ሲወለድ አራት ጊዜ።

3. ማጨስኔ ፋሪእኔ እምዶ ማላሜስ። (ጋሞ)

    ትርጉም፣ ሴትና ፈረስ ያቀረቡለትን ይበላል።

4. ቃራ ዲራ ቃምሶያን ሺአዳ ኩታን ቀጫውስ። (ጋሞ)

    ትርጉም፣ አዋቂ ነኝ ባይ ሴት በቀሚሷ ሽንታ በነጠላዋ ትጠርጋለች።

5. አይረዳ በልዳ ማጫ ናአይ የላይዳ የካውሱ። (ጋሞ)

    ትርጉም፣ እያወቀች የተገናኘች ሴት ስትወልድ ታለቅሳለች።

6. አሲያ አዝና በአዳ በኢሻ ሳራ ጉኤቻ። (ጋሞ)

    ትርጉም፣ ሴት ባልዋን አዝላ ወንድሟን ትጎትታለች።

7. እቃ ግን አጥታ ያዶጋላሶ አቀስ። (ጋሞ)

    ትርጉም፣ ተለምና እንቢ ያለች ሴት በፋቂ ቤት ታድራለች።

8. አሳማቻ ተሚኞ ዋራይ። (ጋሞ)

    ትርጉም፣ የሰው ሚስት የሚስቴን ወገብ ትበጥሳለች። /ሴት ስትወለድ/

9. ማጨስ ሀይቃ ኢሳ። (ጋሞ)

    ትርጉም፣ ሴት ሙት ናት።

10. ሀመተናይ ጌዳ ጌዶ ሀሰናይ ማጫ ሰራይ ጊዳ። (ወላይታ)

    ትርጉም፣ የሚጓዝበት በሴት ላይ ሆኖ ረጅም መንገድ ይሁን።

11. ማጨ አስ ወዝናይ ጋሼ አይፈኬናሽን አካጣይን ከያስ ቤስ። (ጋሞ)

ትርጉም፣ የሴት ልብ የጤፍ ያህል ነው እሱም ጠፍቶ ፍለጋ ይወጣል።

12. ማጫ አዝና ምርኮያ ጌሌስ። (ወላይታ)

ትርጉም፣ ሴት ባልዋ ሲሞት ጠላቱን ታገባለች።

13. ማጫ የላይ ቀንቃስ።(ወላይታ)

ትርጉም፣ ሴት የወለደ ይደኽያል።

14. ማጫ አሰኒ ባለ ኔኔ አሰዋ። (ወላይታ)

ትርጉም፣ ሴት ልጅና ሰይጣን አንድ ናቸው።

15. ማጨስ ወዝና ትራን ወልደ ባደና። (ወላይታ)

ትርጉም፣ የሴት ልጅ ልብ በደረትዋ እንደወደቀ ጡት ነው።

16. ጨናው ባንጊ ናኦ ሚጭ ዬጌፓኮ። (ወላይታ)

ትርጉም፣ የሴት ልጅ ስህተት ነውሯ ነው።

17. ማጫይ ቱና። (ወላይታ)

ትርጉም፣ ሴት እርኩስ ናት።

18. ማጫ ኤሮ አንድያን ፐሌቶ። (ወላይታ)

ትርጉም፣ ሴት ትወቅ በወንድ ያልቅ።

19. አዝናይ አጢዬ ማችዬ ቻዬ ጡቀርስስ። (ጋሞ)

ትርጉም፣ ባልዋ የጠላት ሴት ቅማል በእርግጫ ይመታታል።

20. ማጫ ዶቐይ ፑቴና። (ወላይታ)

ትርጉም፣ ሴት ያሳደገው አይረባም።

<<ሴት በቆመችበት ሳር አይበቅልም፡፡>> የሚለው ማር ጡትዋን አጥብታ የምታሳድገዋን ወላጅ እናት ከድርቅ ጋር ስትመሰል እናያለን፡፡ በየትም ሥፍራ ብትሄድ ወይም በተገኘችበት ሁሉ ረሀብ እንደሚሆን ያስረዳናል፡፡

<<ሴት ስትወለድ ሦስት ጊዜ እልል በሉ ወንድ ሲወለድ አራት ጊዜ>> ወላጅዋን የዘጠኝ ወር ቤት ተፈጥሮ እንኳን ከሁሉ አስበልጣ ለሰው መፈጠሪያ ሰው ወደዚች አለም ከመምጣቱ በፊት ሙሉ አካሉን የሚይዝበትን የሰው መቆያ ወርቅ ማህፀን ከእግዚአብሄር የተቸረችው ሴት ናት፡፡ ይህንን እንዴት መረዳት ተስኖን ነው፡፡ ስትወለድ ክብር የነፈግናት፡፡

<<ሴትና ፈረስ ያቀረቡለትን ይበላል>>ከሰው የተለየች ፍጡር አይደለችም፡፡ ሰው እንደሚመገበው ትመገባለች፡፡ ሆኖም ግን የማትመርጥ ያገኘችውን የምታግበሰብስ ሆዳም ተደርጋ እንደ ጋማ ከብት ስትበላ የምትውል መሆንዋን ይገልፃል፡፡ ጠለቅ ብለን ስናይ ግን አብዛኛውን ጊዜዋን ሠርቶ በማብላ ነው፡፡ የምታሳልፈው፡፡

<<አዋቂ ነኝ ባይ ሴት በቀሚሷ ሽንታ በነጠላዋ ትጠርጋለች>> ይህ ከእውነት የራቀ ምሳሌ ነው፡፡ ሰው እያወቀ ሲሄድ የተሻለ ነገር ይሠራል፡፡ እንጂ የእራሱን ንጽህና መጠበቅ አያቅተውም፡፡ የምሳሌው መልእክት ግን በሴቷ ላይ እጅግ ፀያፍ ነገርን ያስተላልፋል፡፡ ይህ የሚያሳየን ሴትዋ በአካል ብቻ ሳይሆን በቃላትም ስትጠቃ እንደኖረች ነው፡፡

<<እያወቀች የተገናኘች ሴት ስትወልድ ታለቅሳለች>> ይህ ደግሞ የሚገርም ነው፡፡ የተፈጥሮ ግዴታዋን ምንታድርግ፡፡ ለጋራ ጉዳያችን አብረን መጨነቅ ሲገባን፤ የወለደችውን አቅፈን ስንስም ደስ እያለን ችግርዋን እንደችግራችን አለማየታችን አሳዛኝ ነው፡፡

<<ሴት ባልዋን አዝላ ወንድሟን ትጎትታለች>> ይህንን የምታደርገው ወንድምዋን ለመጉዳት ሳይሆን ወይም ሽክም አምሮአት ሳይሆን አማራጭ ስለሌላት ነው፡፡ ምክንያቱም ወንዶች ሚስቶቻቸውን እንደ ግዞተኛ ስለሚያዩአቸው የፈለጉትን እንዲሰሩ ያደርጋሉ፡፡ እንቢ የማለት ነፃነት የላትም፡፡

<<ተለምና እንቢ ያለች ሴት በፋቂ ቤት ታድራለች>> የማይመቻት ወይም በማትፈልገው ነገር ይሆናል:: ያለመፈለግዋን የገለፀችው ከተጠየቀች እንቢ ማለት ስለሌለባት ብቻ ለማጥላላት የተነገረ ነው፡፡

<<የሰው ሚስት የሚስቴን ወገብ ትበጥሳለችች፡፡>> /ሴት ስትወለድ/ ይህ ደግሞ ሴት ልጅ ስትወለድ በአባትዋ የሚነገር ምሳሌያዊ ንግግር ነው፡፡ አባት የገዛ ልጁን ሴት በመሆኗ ብቻ ሲነቅፋት ስናይ ሴቶች በመወለዳቸው ያለው ጥላቻ ከፍተኛ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡

<<ሴት ሙት ናት፡፡>> የሚለው ምሳሌያዊ ንግግር ደግሞ ሴትን ከሞተ በድን ጋር አንድ ያደርጋል፡፡ ከሁሉም በላይ በሁሉም ሥፍራ ቀድማ የምትገኝ በአብዛኛው የስራ ገፊት ቀማሽ ደከመኝ ሰለቸኝ የማትል ቤተሰብዋን አፍቃሪ መጋቢ፣ አስተዳዳሪ ልጆችዋን በስነ-ምግባር በማነፅ በቅድሚያ ኃላፊነት ወሰዳ የምታሳድገዋን እናት ምንም እንደማትጠቅም ተደርጋ መወሰድዋን ያስገነዝባል፡፡

<<የሚንዝበት በሴት ላይ ሆኖ ረጅም መንገድ ይሁን፡፡>> ይህ ደግሞ ትረገጥ፣ ትጨቆን፣ ትሰቃይ የሚል ነው፡፡ ምን ባጠፋች ያለእረፍት ቤተሰቦችዋን አገልጋይ ሆና እያለች ስቃይዋን እንዲበዛ ማድረግ የለብንም፡፡

<<የሴት ልብ የጤፍ ያህል ነው፡፡ እሱም ጠፍቶ ፍለጋ ይወጣል፡፡>>የሚለው ሴቶች ልበ ቢስ እንደሆኑና ምንም ነገር ማስታወስ የማይችሉ ቁም ነገር የሌላቸው ከንቱዎች መሆናቸውን የሚያስረዳን ነው፡፡

<<ሴት ባልዋ ሲሞት ጠላቱን ታገባለች፡፡>> የሚለው የሴቶችን ክፋት፣ ጭካኔ፣ ክህደት የሚገልጽና ለቤተሰብዋ የማታስብ እንደሆነች የሚነግረን ነው፡፡ ይህን ስል ከባለቤትዋ ጋር አብረው ሲኖሩ ልጆች ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ልጆችዋንም ለጠላት አሳልፋ መስጠትዋን የሚያስረዳ ነው፡፡

<<ሴት የወለደ ይደኸያል፡፡>> የሚለው ደግሞ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ሴትን መውለድ ችግር፣ ድህነት መሆኑን ያስረዳል፡፡ ምርታማ ለመሆን መተኪያ የሌለውን የሰው ኃይል ወላጅ የሆነችዋን ሴት እሰየው እንኳን ተወለደች ብሎ እንደመቀበል ጭራሽ ከድህነት ጋር መቆራኘትዋን የሚያመለክተን ነው፡፡

<<ሴት ልጅና ሰይጣን አንድ ናቸው፡፡>> ሴትን ከሰይጣን ጋር አንድ ያደርጋታል፡፡ የምትሠራው ሁሉ በክፋት የተሞላ ምንም ጥሩ ነገር የማትሠራ ተንኮለኛ መሆንዋን ይነግረናል፡፡

<<የሴት ልጅ ልብ በደረትዋ እንደ ወደቀ ጡት ነው፡፡>> የእናት ጡት ልጅን ለማሳደግ ከምንም በላይ ንፅህናው የተጠበቀ ነው፡፡ አቀማመጡም የተፈጥሮ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ አባባል እንደማይጠቅም ሆኖ ተወስዷል ልቧም እንደዚያው የወደቀ የማይሠራ እንደ ሆነ ይገልፃል፡፡

<<የሴት ልጅ ስህተት ነውሯ ነው።>> ስህተት መፈፀም እንደሌለባት እና ከተሳሳተች መዋረድዋ ነው። ይላል ፍፁም እግዚአብሄር ብቻ ነው። የሚሰራ ሰው ይሳሳታል። ምነው መሳሳት ሴቷ ላይ እንደ ነውር ተቆጠረ።

<<ሴት እርኩስ ናት።>> ምነው እርኩስ መሆንዋ የአለምን ፈጣሪ  የወለደችው እኮ ቅድስት ድንግል ማርያም ነች ይህንን ዘንግተን ነው ሴት ከእርኩስ የተመደበችው።

<<ሴት ትወቅ በወንድ ያልቅ።>> ይህ ማለት ሴቶች ምን እውቀት ቢኖራቸው በወንዶች ካልተደገፉ ውጤታማ አይሆኑም እራሳቸውን ችለው መቆም አይችሉም። ብቃት የላቸውም በማለት ዘወትር ጥገኛ እንደሆኑ ወንዶችን ጠንካራና ሊቅ ሴቶችን ደካሞች በማድረግ ሚገልፅ አባባል ነው።

<<ባልዋ የጠላት ሴት ቅማል በእርግጫ ይመታታል።>> ስትጠላ መጥላት የምትችል የሰው ፍጡር ሆና እያለ ከተባይ ጋር ትመሰላለች። ባልዋ ከጠላት መጥላትና መተው ስትችል ምንም ማድረግ የማትችል ደካማ እንደሆነች ይገልፃል።

<<ሴት ያሳደገው አይረባም።>> ልጅ የሚያድገው በእናቱ እንክብካቤ የእናቱን ጡት እየጠባ ሁሌ ክትትል እያደረገችለት ነው። በስነምግባሩም ቢሆን ከልጅነት እስከ እውቀት ሲያጠፋ እየተመከረ ነው። ምሳሌው የሚለው ግን ሴት ካሳደገችው ብልሹ ይሆናል ነው። ምነው ከወለደች በኋላ ተቀብሎአት የሚያሳድግ ብታገኝ ድካም ይቀልላት ነበር።

3.4. **በወላይታና ጋሞ በወንዶች ላይ አዎንታዊ ተባልጦ የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ትንተና።**

1. አልኦ አዝና ባእድ ጋጨተስ። (ጋሞ)

    ትርጉም፣ በመከራ የተገኘን ባል አዝለው ይፈጫሉ።

2. ቢይናአይ ቢዲንቴና አቃሲና አይ ቲጌትስ። (ጋሞ)

    ትርጉም፣ የሴት ልጅ አመድ የወንድ ልጅ አለት።

3. ሀና እያ ጊታ ዲኮ ታናዬ ኤክሸን አትስ። (ጋሞ)

    ትርጉም፣ እኔ ትልቅ ብሆን አገባት ነበር። /ወንድ ለአቅመ አዳም ሳይደርስ መመኘት ይጀምራል /።

4. ማጫ ወዘናይ እስኖ አዴይ ላፑይ። (ጋሞ)

    ትርጉም፣ የሴት ልጅ ልብ አንድ ናት የወንድ ልጅ ሰባት።

5. ናአይ ቢዲንሶ ናአ ቴጌልሶ።(ወላይታ)

ትርጉም፣ የወንድ ልጅ ጉትቻ ነው የሴት ልጅ አመድ ናት፡፡

6. ማጫ ማጀትያ አዴ ዳንዶን፡፡ (ወላይታ)

   ትርጉም፣ ሴት በማጀት ወንድ በችሎት፡፡

7. ማጫ ኦሮ አድያን ፐሌቶ፡፡ (ወላይታ)

   ትርጉም፣ሴት ትወቅ በወንድ ያልቅ፡፡

8. ማጫ ኪቲይ ሃይቆያየና፡፡ (ወላይታ)

   ትርጉም፣ ሴት የላከው ሞት አይፈራም፡፡

9. ሲቅዬ ነአማቺያ ቦሌዋ ሲታን ከሎ ዱራውሱ፡፡ (ወላይታ)

   ትርጉም፣ የሚወዱት ልጅ ሚስት አማቿ ፊት ራቁትዋን ትጨፍራለች፡፡

<<በመከራ የተገኘን ባል አዝለው ይፈጫሉ፡፡>> የሚለው ወንድን ለማግኘት በጣም መልፋት መውጣት መውረድ እንደሚያስፈልግ ከተገኘም በኋላ እድሜ ልኩ እሹሩሩ መባል እንዳለበት እንዲሁም ወንዶችን ከፍ አድርጎ ማየትና ለሴቶች የሚሰጠው ግምት ዝቅተኛ መሆኑን ያስረዳናል፡፡

<<የሴት ልጅ አመድ የወንድ ልጅ አለት፡፡>> የሴት ልጅን ጠንካራ አለመሆን ያሳየናል፡፡ ከምትሰራው ዘርፈ ብዙ ስራ አንጻር ሲታይ ለጥንካሬዋ መግለጫ አይደለም አለት ብረት መባል ነበረባት፡፡ ሆኖም ግን ሴትዋን ደካማ ወንዱን ጠንካራ የማይበገር አድርጎ ያሳየናል፡

<<እኔ ትልቅ ብሆን አገባት ነበር፡፡>>እዚህ ላይ ደግሞ የሚያሳየን ወንዱ እድሜው ሳይደርስ ለጋብቻ እንደሚመኛት ሲሆን ሴቷ የመመረጥ እንጂ የመምረጥ አቅም እንደሌላትና ለማግባት እንደምትገደድ ያመላክታል፡፡

<<የሴት ልጅ ልብ አንድ ናት የወንድ ልጅ ሰባት፡፡>> ሴትና ወንድ አንድ አይነት አፈጣጠር እያላቸው ሴትዋን ለማሳነስ ወንዱን ከፍ ለማድረግ የተነገረ ምሳሌ ነው፡፡

<<የወንድ ልጅ ጉትቻ ነው የሴት ልጅ አመድ ናት፡፡>> ይህ ደግሞ የማትረባ ቆሻሻ ነገር ተደርጋ ስትወሰድ ነው፡፡ መቼም ለጠሉት ነገር ጥሩ ስም የማይሰጥ ሆኖ እንጂ እንኳን ለቤተሰብዋ ማህበራዊ ኑሮውን አድማቂ እሷው ነበረች፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ወንድን ጌጥና ውብ አድርጎ ያስቀምጠዋል፡፡

<<ሴት በማጀት ወንድ በችሎት፡፡>>ይህ ደግሞ ሴቶች ሁል ጊዜ ውሎአቸው በማጀት ብቻ ተወስኖ መቅረት እንዳለበት ሆኖ ወንዶቹን ግን ፈላጭ ቆራጭ አድርጎ ከፍያለ ቦታ ያስቀምጣቸዋል፡፡ ይህ ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ እንግዳ 1999 አዲሱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፡፡ አስቴር ነጋ የግል ማተሚያ ቤት እንደገለፁት

በድሮ ስርዓት ሴቶች በዝቅተኝነት ይታዩ እንደነበርና ለቤት ውስጥ ሥራ ብቻ የተፈጠሩ ተደርገው እንደሚወሰዱ አመልካች ነው፡፡

<<ሴት ትወቅ በወንድ ያልቅ፡፡>> ይህ ማለት ሴቶች ምን እውቀት ቢኖራቸው በወንዶች ካልተደገፉ ውጤታማ አይሆኑም እራሳቸውን ችለው መቆም አይችሉም፡፡ ብቃት የላቸውም በማለት ዘወትር ጥገኛ እንደሆኑ እና ወንዶችን ጠንካራና ሊቅ ሴቶችን ደካሞች በማድረግ የሚገልፅ ነው፡፡

<<ሴት የላከችው ሞት አይፈራም፡፡>> ይህ ደግሞ የወንዶችን ጀግንነት ምንም የማይፈሩ መሆናቸውን ይገልፃል፡፡

<<የሚወዱት ልጅ ሚስት አማቿ ፊት ራቁቷን ትጨፍራለች፡፡>> በቤተሰቡ የሚወደድ የወንድ ልጅ ሚስት ሳትፈራ ሳትጨነቅ ትኖራለች፡፡ እሱ ከተጠላ ግን የሷ ጥላቻ እጥፍ ይሆናል፡፡

3.5. **በወላይና ጋሞ በወንዶች ላይ አሉታዊ ተባልጦ የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮች፡፡ ትንተና፡፡**

1. ቦሎ ዳለ ዳይ ማቾ ኤኬስ፡፡(ጋሞ)
   ትርጉም፣ አማቹን የወደደ ሰነፍ ሴት ያገባል፡፡
2. ገሙ መቼ ጉዶይ ላሞቲድ ከሴና፡፡ (ጋሞ)
   ትርጉም፣ ሁለት ሚስት ያለው እርካታ የለውም፡፡
3. አዝና ጋቤ መቾቲ ከራይ ሀኬኔ፡፡ (ጋሞ)

   ትርጉም፣ የባልዋን ድክመት ገበያ ላይ ያየ እደጅ መጥቶ ሚስቱን ይደበድባል፡፡
4. ካሪ ባይና ካናይኔ ማጤስ ባይድ መሰንተይ እስዋ ፡፡ (ጋሞ)

   ትርጉም፣ ቤት የሌለው ውሻ ሚስት የሌለው ለማኝ፡፡
5. ወዝና ወርን አዝናይ የዴስ፡፡ (ወላይታ)

   ትርጉም፣ ልበ ጎዶሎ ባል ይፈታል፡፡

<<አማቹን የወደደ ሰነፍ ሴት ያገባል፡፡>> ቤተሰቦችዋን በመውደዱ ብቻ ሳይወዳት ሰነፍዋን ሴት ማግባቱን ይገልፃል፡፡ ይህን ያደረገው የቤተሰቦችዋን ሀብት አይቶ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ለብር ብሎ ያገባት መሆኑን ያሳየናል፡፡

<<ሁለት ሚስት ያለው እርካታ የለውም፡፡>> ይህ አባባል ወንዶች ሁሉ አማረሾች እረፍት የሌላቸው በአንድ የማይረጉ ያዩትን ሴት ሁሉ የሚመኙ ሴሰኞች መሆናቸውን የሚገልፅ ነው፡፡

<<የባልዋን ድክመት ገበያ ላይ ያየ እደጅ መጥቶ ሚስቱን ይደበድባል፡፡>> የሚለው ሰነፍ ወንድ ሚስቱን የማያስከብራት የሚያስጠቃት አንደሆነ ያስረዳል፡፡

<<ቤት የሌለው ውሻ ሚስት የሌለው ለማኝ፡፡>> ሚስት የሌለው ወንድ ኑሮው የተሟላ አይሆንም ብቸኝነቱ ለብዙ ችግር እንደሚዳርገው ያሳያል፡፡

<<ልበ ጎዶሎ ባል ይፈታል፡፡>> የሚለው ልብ የሌለው ለትዳር የማይስብ ስራ ተግቶ በመስራት ለቤተሰቡ የማይጠቅም ወንድ ለትዳር እንደማይሆንና ከሱ ጋር በትዳር መቆየት አስፈላጊ ያለመሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህ ቆራጥ ሴቶች የሚወስኑት ውሳኔ ነው፡፡

3.6. **በወላይታና ጋሞ በሴቶች ላይ በተመሳሳይ በአሉታዊ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ትንተና፡፡**

1. ማጨስ ማቆስ ማቲሞከና፡፡ (ጋሞ)
   ትርጉም፣ ሴት በቆመችበት ሳር አይበቅልም፡፡
2. ማጨ ኢሳ ደርዶር ኬታን ሳንቲ ኮኤና፡፡ (ወላይታ)
   ትርጉም፣ ሴት በበዛበት ቤት ጎመን አይለመልምም፡፡
3. ማጨስ ላፑና የሊድ ጨራራ ጉፔስ፡፡ (ጋሞ)
   ትርጉም፣ ሴት ሰባት ወልዳ አጥር ትዘላለች፡፡
4. ግጌና ጊ አቃዳ ያውሱ፡፡ (ወላይታ)
   ትርጉም፣ የማትረባ ሴት ውጪ አድራ ትመጣለች፡፡

በጋሞ <<ሴት በቆመችበት ሳር አይበቅልም፡፡>> ሴቶች የቆሙበት ወይም የተገኙበት ቦታ ድርቅ ይሆናል የሚል ነው፡፡

በወላይታ <<ሴቶች በበዙበት ጎመን አይለመልምም፡፡>> ይህ ጎመን ብቻ እንደማይበቅል ቢገልጽም ያው በመጠኑ ድርቅ አለ ማለት ነው፡፡

ምሳሌዎቹ የሚያሳዩን ሴቶች ባሉበት ስፍራ ድርቅ መኖሩን ነው፡፡

ጋሞ <<ሴት ሰባት ወልዳ አጥር ትዘላለች፡፡>> ይህ ምሳሌ የልጆች እናት ሆና እፍረት የላትም ዝሙት ትፈፅማለች ማለት ነው፡፡

ወላይታ <<የማትረባ ሴት ውጪ አድራ ትመጣለች፡፡>> በትዳርዋ ላይ ከማንም ጋር ዝሙት ትፈፅማለች ማለት ነው፡፡ ሁለቱም ምሳሌዎች የሚያነሱት ዝሙት እንደሚፈፅሙ ነው፡፡

<u>ምዕራፍ አራት</u>

4. **ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሣብ**

የወላይታና የጋሞ ብሔረሰቦች ለሴቶች ያላቸው አመለካከት ምን እንደሆነ ለመፈተሽ በዚህ ጥናት መጀመሪያ ለቀረበው የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝትና ከሁለቱም ብሔረሰቦች በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ ትንተና ተካሂዷል፡፡ በዚህ ትንተና መሠረት ከዚህ በታች የመደምደሚያና የመፍትሔ ሃሣብ ቀርቧል፡፡

4.1 **ማጠቃለያ ፣**

ምሳሌያዊ ንግግሮች ሰዎች በንግግራቸው መሀል ጣልቃ እያስገቡ ምሬታቸውን ምኞታቸውን ሀዘን ደስታቸውን ስለሕይወት ያላቸውን አመለካከት ያንፀረርቁበታል፡፡ ሲሉ ዘሪሁን አስፋው 2002 ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ማህበረሰብ ሴቶችን በአጠቃላይ ከመኮነን ይልቅ በሚያበረታቱበት ማበረታታት በሚወቀሱበት መውቀስ ሲገባቸው በአጠቃላይ ልፋታቸውን ከንቱ ማድረግ አስፈላጊ ባለመሆኑ ለሴቶች ያላቸውን ዝቅተኛ አመለካከት በመለወጥ ሴቶች ለማህበሰረቡ ከሚሰጡት ከፍተኛ ጥቅም አኳያ ቀደም ሲል በሴቶች ላይ በአሉታዊ ይነገሩ የነበሩትን ምሳሌያዊ ንግግሮች የመለወጥ ሥራ መሰራት አለበት፡፡

የዚህ ጥናት የመረጃ ትንተና እንደሚያሣየው አብዛኛዎቹ ምሳሌያዊ ንግግሮች ሴቶችን አጥፊዎች፣ አላዋቂዎች፣ ጨካኞች፣ ደካሞች፣ በስራቸውም፣ በእውቀታቸውም፣ በማንነታቸውም፣ በአስተሳሰባቸውም ህብረተሰቡ ዝቅተኛ ቦታ የሚሰጣቸው መሆኑን አጉልቶ የሚያሳየን ነው፡፡ የሚሰጡትን በርካታ አገልግሎት ከምንም ውስጥ አለማስገባቱ አያሳዝንም ትላላችሁ፡፡ እነዚህን ችግሮች ለወደፊቱ ለማስወገድ ይህ ጥናት የሚከተሉትን የመፍትሔ ሃሣቦች ይጠቁማል፡፡

4.2 **የመፍትሔ ሃሣቦች**

ሀ. ቀደም ሲል  በጽሁፍ የሠፈሩት በሴቶች ላይ የሚነገሩ አሉታዊ

ምሣሌዎች እንደአስፈላጊነታቸው የመለወጥ ሥራ ትኩረት ቢደረግ፡፡

ሕብረተሰቡ በሴቶች ላይ የሚነገሩ አሉታዊ ምሣሌዎች ላይ ግንዛቤ እንዲኖረው በአብዛኛው ምሣሌያዊ ንግግሮች ሴቶችን የሚያናንቁና የሚያጣጥሉ በሠሩትም ባልሠሩትም ነገር ተወቃሾሽ የሚያደርጉአቸው መሆኑን ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ቢሰራ፡፡

ለ. አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በሴቶች ላይ ያለው አመለካከት የተሻለ ቢሆንም በአብዛኛው ስለሴቶች ይነገሩ የነበሩት ምሳሌያዊ ንግግሮች አሉታዊነታቸውን ይዘው ለአዲሱ ትውልድ እንዳይተላለፉ በመማሪያ መጽሐፍት ላይም ሆነ በሌሎች መጽሐፍት ላይ ተጽፈው በሚወጡት ምሳሌዎች ላይ የማስተካከሉ ሁኔታ ትኩረት ቢደረግ መልካም ነው፡፡

ሐ. ከተሰበሰበው መረጃ እንደተገለፀው ማህበረሰቡ በሴቶች ላይ የነበረው አመለካከት ዝቅተኛ መሆን ሴቶች ደካማ የሕብረተሰብ ክፍሎች ስለሆኑ የትም አይደርሱም የሚል አስተሳሰብ የነገሠ ስለነበር በሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ የሕብረተሰቡን አመለካከት በመለወጥ ሴቶች ደራሲዎች፣ ጋዜጠኞች፣ ተዋናዮች ፣ ገበሬዎች ፣ ሐኪሞች ፣ አስተዳዳሪዎች ፣ እናትም እህትም፣ ሀገርም ምንም ነገር ከመሆን የማይታቀቡ ብርቅዬ የሕብረተሰብ ክፍሎች እንደሆኑ በመግለጽ በአሉታዊ ይነገሩ የነበሩት ምሳሌዎች መለወጥ እንደሚገባቸው ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

መ. በዘመናችን የሴቶች እህቶቻችንን ታታሪነት የሥራ ብቃት አገልጋይነት የላቀ አስተሳሰብ ያላቸው መሆኑን የማይገነዘብ የሕብረተሰብ ክፍል አለ ብዬ አላምንም፡፡ ከአሁን በኋላ ግንዛቤአችንን የበለጠ በማዳበር የቃላት ጥቃታችንን ልናነሳላቸው እና ታሪክ ለመቀየር ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡ እላለሁ፡፡

## <u>አባሪዎች</u>

**በጋሞ እና በወላይታ ብሔረሰብ በወንዶችና በሴቶች መካከል አዎንታዊ እና አሉታዊ ተባልጦ የሚያሣዩ ምሣሌያዊ ንግግሮች**

1. ኤሰትያራ ቦራ የሳውሱ፡፡

    ትርጉም ፣ የቸኮለች ሴት በሬ ታልባለች፡፡

2. ማጨስ ማቲሞከና፡፡

    ትርጉም ፣ ሴት በቆመችበት ሣር አይበቅልም፡፡

3. ናአይ ቢዲንስ ናኦ ናአይ ቴጉልስ፡፡

    ትርጉም ፣ የወንድ ልጅ ጉትቻ ነው የሴት ልጅ አመድ ናት፡፡

4. ማጫ ናኢ የሴትን ሄዞን ጊዜ አለል ጌቲ ኦዴ የለቲን አይዱ ጊዜ አለልጊቲ

    ትርጉም ፣ ሴት ስትወለድ ሦስት ጊዜ እልል በሉ ወንድ ሲወለድ አራት ጊዜ፡፡

5. ማጨስኔ ፋሪእኔ አምደ ማለሜስ፡፡

    ትርጉም ፣ ሴትና ፈረስ ያቀረቡለትን ይበላል፡፡

6. ማጨስ ሀይቃ ኢሳ፡፡

    ትርጉም ፣ ሴት ሙት ናት፡፡

7. ማጨ አስ ወዝናይ ጋሼ አይፈኬናሽን አካጣይን ከያስ ቤስ፡፡

    ትርጉም ፣ የሴት ልብ የጤፍ ያህል ነው እሱም ጠፍቶ ፍለጋ ይወጣል፡፡

8. ቃራ ዲራቃምሶያን ሺአዳ ኩታን ቀጫውስ

    ትርጉም ፣ አዋቂ ነኝ ባይ ሴት በቀሚስዋ ሽንታ በነጠላዋ ትጠርጋለች፡፡

9. ቃራ ዳራ ዲያ ቦሎትዬ ቃራጣውስ፡፡

    ትርጉም ፣ አይናውጣ ሴት ምራትዋን ትገርዛለች

10. ማጫስ ላፑና የሊድ ድረስ ጤረራ ጉፔስ፡፡

ትርጉም ፣ ሴት ሰባት ወልዳ አጥር ትዘላለች፡፡

11. ኢሳ መቴኔ ጊሽን ሳዳዬ ገቲ ማቴሲ፡፡

ትርጉም ፣ እመቤቲቱ ምን ይቸግርሻል ስትባል ወስፌ አለች፡፡

12. ታመነቼ ተመስ ባዳ አዝና ገለውስ፡፡

ትርጉም ፣ ታመነች እሳት ልትጭር ሄዳ ባል አገባች፡፡

13. ማንቁም ማጭስያ ዱሬ ገላና ግን ዱሪያ ማጨስያ ማንቋ ገላና ከያሱ፡፡

ትርጉም ፣ የድሃ ሚስት ሀብታም ማግባት ስትመኝ የሀብታም ሚስት ድሃ ትፈልጋለች፡፡

14. አይረዳ በልዳ ማጫ ናአይ የላይዳ የካውሱ፡፡

ትርጉም ፣ እያወቀች የተገናኘች ሴት ስትወልድ ታለቅሳለች

15. ቄስያ ማጫስያ ጪንጫ ዳሪያዳ ኩቱዋ አያፍያራ ከታውሱ፡፡

ትርጉም ፣ የቄስ ሚስት ሞያተኛ ነች ሲኳት ዶሮ ከነአይኑ ሠራች፡፡

16. ኢሲያ አዝና በአዳ በኢሻ ሳራ ጉኤቻ

ትርጉም ፣ ሴት ባልዋን አዝላ ወንድሟን ትጎትታለች፡፡

17. አዎ ሚቾ ሀትሴይ ዱጌሚን አሰፋ ፌዴ ከዮስ፡፡

ትርጉም ፣ እንጀራ እናት ውኃ ወደታች ወስዷት ሰው ወደላይ ይፈልጋታል፡፡

18. ጣለሒ ወልቀጣይድ ማታዬ ብርሽስ፡፡

ትርጉም ፣ ሴት እውነቱ ሲደረስ ታለቅሳለች፡፡

19. አሽካሪያ በጎዳቃማ ደረቃውስ፡፡

ትርጉም ፣ ሠይጣን ምን አቅም ቢያጣ ሴት አታሸንፈውም፡፡

20. ዕቃ ግን አጥታያደጋላሶን አቀስ።

ትርጉም ፣ ተለምና እነቢ ያለች ሴት በፋቂ ቤት ታድራለች።

21. ወዝና ወንቶ ሎልያ ወንተሽን አዘናቆማሱ።

ትርጉም ፣ ልበ ስስ ሴት ከነጋ በኋላ ባልዋን ታቅፋለች።

22. አታ ገላና ጊየራ አይሌ ገላውስ።

ትርጉም ፣ የበለጠ አገኛለሁ ያለች ባሪያ ታገባለች።

23. ከዎ ተሚቾ ጊኒሽን ተከዎ ሚቾ ገውሱ።

ትርጉም ፣ ንጉስ እህቴ ናት ሳይላት እሷ ወንድሜ ነው ትላለች።

24. ዝንነአረ ይያራ ዝንን አናው ቢያሮ ከኒያ ጋውሱ።

ትርጉም ፣ ሽርሙጣ የምትመጣ ሴት ለወደፊት የሚሄደውን ውሻ ትላለች።

25. ቃማ ክያዳ ቢያራ ጋለስ ያሺስ ጋውሱ።

ትርጉም ፣ በምሽት ወጥታ የምትሄድ ሴት ለቀን ያስፈራል ትላለች።

26. ዱሬያና ማችያ ዱሩማዳን አታውሱ ማንኤስና ማጨሲያ ማኘኤዶን ማልአውሱ

ትርጉም ፣ ድሃ የምታደረግ ሴት እንደጨው ትጣፍጣለች ሀብታም የምታደረግ እንደኩይሳ ትገማለች።

27. አሰማቻ ተሚቾ ዋራይ

ትርጉም ፣ የሰው ሚስት የሚሰቴን ወገብ ትበጥሳለች። /ሴት ስትወለድ/

28. አዬ ሚሹ ኩቶይ ቆመስ።

ትርጉም ፣ የሰነፍ ሴትን ብልት ዶሮ ይጭራል።

29. ቀራ ዶሮ ማለቃ ቀሚስያ ሴን ተራ ቃራ።

ትርጉም ፣ አዋቂ ነኝ ባይ ሴት ብልትዋን ታሣያለች።

30. ጌለ እያ ጌሌጋካ ይዳ ፔንጌ።

ትርጉም ፣ የደረሰች ልጃገረድ ደፍ ትረግጣለች።

31. አታማና ማያራ አይሌ ጌላውስ።

ትርጉም ፣ ባል እመርጣለሁ የምትል ሴት ከምራጭ ትወድቃለች።

32. ማጫ አስ ወዘናይ ጋሼ አይፈ ኬናሽን አካጣይን ከያስ ቤስ

ትርጉም ፣ የሴት ልብ የጤፍ ያህል ነው። እሱም ጠፍቶ ፍለጋ ይወጣል።

33. ቦሎ ዳላ ዳይ ማቾ አኬስ

ትርጉም ፣ አማቹን የወደደ ሰነፍ ሴት ያገባል።

34. ገሙ መቼ ጉዶይ ላሞቲድ ከሌና

ትርጉም ፣ ሁለት ሚስት ያለው እርካታ የለውም።

35. አዝና ጋቤ መቾቲ ከራይ ሀኬኔ

ትርጉም ፣ የባልዋን ድክመት ገበያ ላይ ያየ እደጅ መጥቶ ሚስቱን ይደበድባል።

36. ካሪባይና ካናይኔ ማጤስ ባይድ መሰንተይ እስዋ

ትርጉም ፣ ቤት የሌለው ውሻ ሚሰት የሌለው ለማኝ።

37. ኩባ ሀይቆን አጋናራ ዳፋርን የካውሱ።

ትርጉም ፣ ጨርሶ ሲሞት ልትተው ሲደክመው ታለቀሳለች።

38. ማጫ ሰይ ኒዩ ቲማ ጊን የኮስ።

ትርጉም ፣ ሴቶች ሲፈርዱላቸው ያለቅሳሉ።

39. ሳዊያ ሽሎዋ በአን ሚየ ገለስ ጋውስ።

ትርጉም ፣ ጋለሞታ ድር ማዘል ወገብ ያሳምማል ትላለች፡፡

40. አዝናይ አጢዬ ማችዬ ቻዬ ጡቀርስስ፡፡

ትርጉም ፣ ባሏ የጠላት ሴት ቅማል በእርግጫ ይመታታል፡፡

41. ማጫ አሰኒ ባለኔኔ አስዋ፡፡

ትርጉም ፣ ባል እመርጣለሁ የምትል ሴት ከምራጭ ትወድቃለች፡፡

42. ማጫ አሳ አሞት ደይ ሻራ ጉቢደይ

ትርጉም ፣ ሴት ልጅና  ሠይጣን አንድ ናቸው፡፡፡፡

43. ማጫ ኢስ ደርደር ኬታን ሳንቲ ከኤና፡፡

ትርጉም ፣ ሴት በበዛበት ቤት ኀመን አይለመልምም፡፡

44. ሚዳ ጎዶሞተያ ዮሆ ጋካውስ፡፡

ትርጉም ፣ የምትበላ ቡዳ ሴት ለቀሶ ትደርሳለች፡፡

45. ግጌና ጊ አቃዳ ያውሱ፡፡

ትርጉም ፣ የማትረባ ሴት ውጪ አድራ ትመጣለች፡፡

46. ማጫ ማንቄቴስ ካውሽ ቤልሴስ፡፡

ትርጉም ፣ ሴት ታደኸያለች ስድብ ያቃጥላል፡፡

47. ማጫስ ወዝና ትራን ወልደ ባደና፡፡

ትርጉም ፣ የሴት ልብ በደረትዋ እንደወደቀ ነው፡፡

48. ማጫስ አይ ጎቢያ ኮኮቱሳ አሴና፡፡

ትርጉም ፣ ሴት ምንም ብትጎብዝ ምሰሶ አትተክልም፡፡

49. ማጫ አዝና ምርኮያ ጌሌስ፡፡

ትርጉም ፤ ሴት ባልዋ ቢሞት ጠላቱን ታገባለች፡፡

50. ማ ጨይ ቱና፡፡

ትርጉም ፤ ሴት ርኩስ ናት፡፡

51. ማጫይ ቱሳ  ጠሌና፡፡

ትርጉም ፤ ሴት ምሰሶ አልፋ አትሄድም፡፡

52. ኢታ ማጫ ናአ

ትርጉም ፤ ሴት መጥፎ ልጅ ናት፡፡

53. ማጫ አመናይ ኤያ፡፡

ትርጉም ፤ ሴትን ያመነ ሞኝ ነው፡፡

54. ማጫ ወዘን ከቆን ፔኢስ፡፡

ትርጉም ፤ የሴት ልብ ተንጠልጥሎ ይውላል፡፡

55. ሜጫ ወዘን ቶታ፡፡

ትርጉም ፤ የሴት ልብ ሥርዓት የለውም፡፡

56. መጨናው ባንጋ ናአ ሚጭ ዬጌፖኮ፡፡

ትርጉም ፤ የሴት ልጅ ስህተት ነውሯ ነው፡፡

57. ጫለና ኢትየራ ዱረናው ኤቃውሱ፡፡

ትርጉም ፤ ሴት ልጅ ስትጫወት አያምርባትም፡፡

58. አዋቅያ ማችያ አዝና ዋጉዋ ዲጋሉሱ፡፡

ትርጉም ፤ ቀበጥ ሚስት የባልዋን ሬሳ ከቀብር ትከለክላለች፡፡

59. ሲዋያ ሚኒጣፈ ቁም ኤስ ጋውስ፡፡

ትርጉም ፧ ጋለሞታ ምንጣፍ ይቆረቁራል ትላለች፡፡

60. ማጫ ጊዳ ኡታ ሼአ፡፡

ትርጉም ፧ እንደ ሴት ተቀምጠህ ሽና፡፡

61. ማጫ ድቾ ይ ፑቴና፡፡

ትርጉም ፧ ሴት ያሳደገው አይረባም፡፡

62. ወዘና ወርን አዝናይ የዴስ፡፡

ትርጉም ፧ ልበ ጎዶሎ ባል ይፈታል፡፡

63. አዲስ ግኮ ማጫናይ አይሰሱ

ትርጉም፧ ሁኔታው ከፈቀደላት ሴት ታስተዳድራለች

64. ኩቶ ሹኪን አሾ ኩሼ አይኪን መቾ

ትርጉም ፧ ዶሮ አርደው ሥጋ በእጅ ይዘው ሚስት

65. ጦስ ጦሬ እምን አማራ ቀንጢ ከኤስ

ትርጉም ፧ እግዚአብሔር የፈጠረውን የሴት ብልት አማራ ቆርጦ ይጥላል፡፡

66. አዋይ ዶሲያ ናአይ ሳይታውሱ

ትርጉም ፧ አባትዋ የሚወዳት ልጅ ፊት ትሆናለች፡፡

67. አልኦ አዝና በእድ ጋጬተስ

ትርጉም ፧ በመከራ የተገኘን ባል አዝለው ይፈጫሉ፡፡

68. ቢይናአይ ቢዲንቴና አቃሲና አይ ቲጌትስ፡፡

ትርጉም ፧ የሴት ልጅ አመድ የወንድ ልጅ አለት፡፡

69. በፒአቲን በመቼስ አቲሪ ባቲስ፡፡

ትርጉም ፣ እራሱ አጥፍቶ ሚስቱን ተጠያቂ ያደረጋል፡፡

70. ገልመይ ያደኖ ጪማ ካኪቴ ወደተኔ

ትርጉም ፣ ጠብደል ጎረምሳ ያረጠች አሮጊት ያሰረግዛል፡፡

71. ናአይ ቢዲንስ ናኦ ናአይ ቴጉልሶ፡፡

ትርጉም ፣ የወንድ ልጅ ጉትቻ ነው፡፡ የሴት ልጅ አመድ ናት፡፡

72. ሀናእያ ጊታ ዲኮ ታናዮ ኤክሽን አትስ

ትርጉም ፣ እኔ ትልቅ ብሆን አገባት ነበር፡፡ /ወንዱ/

73. ማጫ ወዘናይ አስኖ አዴይ ላፑና፡፡

ትርጉም ፣ የሴት ልብ አንድ ናት፡፡ የወንድ ልብ ሰባት፡፡

74. ማጫ ማጀትያ አዴ ዳነደን፡፡

ትርጉም ፣ ሴት በማጀት ወንድ በችሎት፡፡

75. ማጫ ኤሮ አንድያን ኘሌቶ፡፡

ትርጉም ፣ ሴት ትወቅ በወንድ ያልቅ፡፡

76. ማጫ ኪቶይ ሂይቆ ያዩና፡፡

ትርጉም ፣ ሴት የላከው ሞት አይፈራም፡፡

77. ሲቅዮ ነአ ማቺያ ቦሎዋ ሲታን ከሎ ዱራውሱ፡፡

ትርጉም ፣ የሚወዱት ልጅ ሚስት  አማቷ ፊት ራቁትዋን ትጨፍራለች፡፡

78. አይሴራ አይሲዳ አይም ዳሜራ ኤፍ ዳኘስኮ፡፡

ትርጉም ፣ ከቀይ ሴት ጋር ሕልም ከጠይም ሴት ጋር እንቅልፍ፡፡

79. ኩበቀሪያ የውከረን ሱቃውሱ፡፡

ትርጉም ፤ እጅግ ስልጡን ለቀሶ መሀል ትፈትላለች፡፡

80.. ማጫ ሞገሰና ቦና፡፡

ትርጉም ፤ ሴት ወደቀብር አትጠጋም፡፡

81 . ማጫ ሄዩ ቱማ ግን የኬሳ፡፡

ትርጉም ፤ ሴት እውነቱ ሲደረስ ታለቅሳለች፡፡

82. ባቁሊያ ወደሩዋ ዱታሰ ጊን ባው ቃን ታውሱ

ትርጉም ፤ በቅሎዋ ገመድ በጠሰች በራሷ አሳጠረች፡፡

83. ኦዱሩዋኮ ሺቅዳ አክራሳይ ኡባ ውዴ ዬካስ

ትርጉም ፤ ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ሁሌ ያለቅሳል ፡፡

84. ካሮ ከታ ማናፔ ላጢ ኡታ ሚዮጌ ዳሬስ

ትርጉም ፤ የነገን በማሰብ የዛሬን አለመጣል፡፡

85. ጣሊያ ለፋ ኡይድቶሁዋ ማሌቴስ

ትርጉም ፤ የራስን ጥፋት በሰው ማሳበብ፡፡

86. ማርፔ አቴናይ ማረ ባይዜስ

ትርጉም ፤ መርፌ የማያስገባ ጥድ ይሸጣል፡፡

87. ባውታ  ሚዮ ሼንያን አቶ ኩሜታ

ትርጉም ፤ ጥንብ ከበሉ እንሥራ ሙሉ፡፡

88. ማታዬ ናታኔ ዘዙዬ ናታ ዴታን ሻካና

ትርጉም ፤ በወተት ያደገና በቦርዴ ያደገ ዳገት ላይ ይለያል፡

## ዋቢዎች


**መንገሻ ግዛው፡፡** (1973) ‹‹የወላይትኛ ተረትና ምሣሌዎች ›› በአዲስአበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ-ጽሁፍ ለባቺለር ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

**ሰለሞን ታደሰ፡፡** (1986) ‹‹ የአማርኛና የኦሮምኛ ምሣሌያዊ ንግግሮች በንጽጽራዊ ጥናት›› አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ለባቺለር ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

**ወርቁ ከበደ፡፡** (1973) ‹‹ የሶማሊኛ ተረትና ምሣሌዎች›› አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ለባቺለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

**ደበበ ኃ/ጊየርጊስ እንግዳ፡፡** (1999) <u>አዲሱ ምሣሌያዊ አነጋገሮች</u>፡፡ አስቴር ነጋ የግል ማተሚያ ድርጅት፡፡

**ዘሪሁን አስፋው፡፡** (1992) <u>የሥነ-ጽሁፍ መሠረታዊያን</u>፡፡ አደስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

**Les Law** (1973) <u>English Amharic Context dictionary</u>, wies Baden harrassowitz

**Mider, Wolfgang** (2004) <u>proverbs a hand book green wood</u> press

**Simpson Jon** and Speakesennifer (1998), <u>oxford concise dictionary of proverbs</u> Oxford University press.

**Stone, Son R** (2006) <u>the Rout ledge book world proverb</u> newyourk Rout laedge